


ስለ-ሲ

ስለ - ሲ
ስለ - ኬ
ስለ - ኦንቹ
ስለ - ሁለቹን
ኦየተዘጋጀኩ የምጫወርብ

ስለ - ሲ 05 ላላኬ/2012

መግቢያ

ሰለ-ሷ በየወሩ በሴቶች ጥንካሬ ፣ ፈተና እና ድል ዙሪያ እየተሰናዳች የሚትቀርብ ህትመት ናት።
የህትመት ሥራዋ ሴትነትን ከፍ በማድረግ ከህልማቸው እና ከስኬታቸው የደረሱ ተምሳሌቶችን ታርክ በይዘታቸው አሰውባ ለአንባቢዎቿ ታቀርባለች።

ለአንባቢያን መቅረብ ከጀመረች ሰድስት ወር የሞላት ሲሆን ባለፉት አምስት ወራት አራት ህትመቶችን ወደ እናንተው ውድ አንባቢያን አድርሳለች። ይህችም የዓመቱ የመጨረሻ አምስተኛ ህትመታችን ናት። በህትመቷም ቀደም ካሉ ህትመቶች የተመረጡ ሁለት ገጾችን አቅርበንላችኋል።

ያለፉትን ህትመቶች በእናንተው አንባቢያን ሃሳብ በየወሩ ለማሻሻል የሞከርን ቢሆንም ይበልጥ በተሻለ መልኩ ከአድስ ዓመት ጀምሮ ይዘን ለመቅረብ ቅድመ ዝግጅት በማድረግ ላይ እንገኛለን ፤ በዚሁም አብራቹን መሰራት እና ሥራዎቻችሁን ማቅረብ የምትፈልጉ በመልዕክት መቀበያ አድራሻችን በማግኘት መሳተፍ የሚትችሉ መሆኑን ከወዲሁ ልናሳውቃችሁ እንወዳለን።

አድስ ዓመትን በአድስ ገጽ በተሻለ ዝግጅት አብረን እንዘልቃለን።

ከዝግጅት ክፍላችን!



ያዝጋጅት ክፍል

ያማኙን ፦ @Sileesua

@Sileesuabot

መልካም ንባብ ይሁንላችሁ . . .

ስለ - ሷ

ሴትነትን ከፍ አድርጋ የብርታት እና የጥንካሬ ምልክትነቷን ስለምታሳየዋ ስለሷ እናነሳለን።



ሳህሌወርቅ ዘውዴ
የኢፌዴሪ ፕሬዝዳንት

በሀገራችን የስልጣን ከፍታ ከሁሉ ልቃ ርዕሰ ብሄር ሆናለች። በዕውቀት የተሞላ ረጅም የሥራ ህይወትን የያዘ ጭንቅላት ባለቤት ናት። የተሰጣትን ሥራ በስኬት ማጠናቀቅ የእርሷ ባህሪይ ነው። የአሁኗ የኢፌዴሪ ፕረዝዳንት የሀገርቱ ርዕሰ ብሔር ሳህሌወርቅ ዘውዴ ትምህርቷን አድሰ አበባ ሊሴ ገብረ ማሪያም ትምህርት ቤት የጀመረች ሲሆን ከፈረንሳዩ ሞንቴፔለ ዩኒቨርሲቲም በጥሩ ውጤት ተመርቃለች። በዩኒቨርሲቲው መልካም ስነ-ምግባርን በመላበስ ትኩረቷን ወደ ትምህርቷ በማድረጓ ከትምህርቷ መልስ የህይወቷን የከፍታ ጉዞ በድል ጀምራዋለች።

“እኛ ሴቶች ዕድሉን ካገኘን ከስኬት ማማ የምያቆመን አንዳች ነገር የለም።” እያለች የውጤታማነት ግስጋሰዋን ቀጠለች። ለመጀመሪያ ጊዜም በሴኔጋል የኢትዮጵያ አምባሳደር በመሆን ማገልገል ጀመረች ይሄውም በጅቡቲ የቀጠለ ሲሆን በተጨማሪም በወቅቱ የምሰራቅ አፍሪካ የልማት በይነ መንግስታት ድርጅት (ኢጋድ) ቋሚ ተወካይም ነበረች። ከዚህም ባሻገር በፈረንሳይ የኢትዮጵያ አምባሳደር እንድሁም የተባበሩት መንግስታት የትምህርት የሳይንስና የባህል ተቋም ተወካይ ፣ በተባበሩት መንግስታት የአፍሪካ ህብረት ቢሮ ኃላፊ እና ተጠሪ ሆና ለበርካታ ዓመታት አገልግላለች።

ይህን ጥንካሬዋን እና ብርታትዋን ሳትገታ በብዙ ተልዕኮዎች ስኬታማነትን ያረጋገጠች ፣ የ2018 እና 2019 የዓለማችን ተጽዕኖ ፈጣሪ ሴቶችን ክብር ያገኘች እርሷ አሁን ላይ በምትወዳት ሀገሯ ለታላቅ ክብር በቅታ የመጀመሪያዋ ሴት ፕረዝዳንት ሆናለች። በኢትዮጵያ ብቻ ሳይሆን አሁን ላይ በመላው አፍሪካ ብቸኛዋ መንበረ ስልጣን ላይ ያለች ሴት ፕረዝዳንት የአገር መሪ ናት።

ሴትነትን ከፍ አድርጋ <<ስለ ሴቶች ጉዳይ ማንሳት ከክፍለ ዘመኑ ጀምሮ ያላለቀ አሁንም የቀጠለ ጉዳይ ነው።>> በማለት ትሞግታለች። ሴትነት ገደብ የለለው መቆሚያ የማይበጅለት የፅናት ውጤት መሆኑን ታሰረዳለች። በእርሷ ልክ ለሎችን ማየት አስደሳች ብቻ ሳይሆን ትክክል ነው ትለናለች እርሷ። ስለሷ ያነሳንላት እርሷ የኛ ተምሳሌት ናትና በእርምጃችን እሷን በማየት ነገያችንን በስኬት እናጅበዋለን።



"እኛ ሴቶች ሰጭኩን ካገኘን
ከስኬት ጣጣ የጣያቀጠን
አንድች ነገር የለም።"

ለሐ - ሷ 01 መጋቢት / 2012 ዓ/ም

ሰለ-ኗ

የሰው ልጆች ጤና ሲጋት ውሰጥ በገባበት ሰዓት ለራሷ ሳይሆን ለመላዊ ኢትዮጵያዊ ጤና ባለማቋረጥ ከፊት ሆና በመሥራት ላይ ስለምትገኘው ብርቱና ታታሪ ሴት ስለ-ኗ እናነሳለን።



እኗ በ1976 ዓ.ም በአድስ አበባ ከተማ በጤና እና በትምህርት ዘርፍ ከተሰማሩ ቤቴሰቦች ተወለደች።

“ልጅ ሆኜም የጤና ዶክተር እንደሚሆን አውቅ ነበር” የምትለዋ የዛኔዋ የእቴጌ መነን ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ባለ ከፍተኛ ውጤት ጎበዟ ተማሪ የዛሬዋ የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሴ። የሁለተኛ ደረጃ ትምህርቷን እንዳጠናቀቀች በወቅቱ ከነበሩት ሶስት የጤና ትምህርት ቤቶች ወደ ጅማ ዩኒቨርሲቲ ጤና ትምህርት ቤት ተመደበች። በትምህርት ቤቱ የሴቶች ቁጥር ማነስ ትከነከን እና ያሳስባት ነበር።

ዶ/ር ሊያ የጤና ዶክተር መሆን እንዲሁ ስራ ብቻ አይደለም በማለት የህይወቷ ጥልቅ ስሜት ማረፊያ እንደሆነም ትናገራለች። በተጨማሪም በወሊድ እና የማህፀን ህክምና ተባባሪ ፕሮፌሰር ስትሆን በዚህም እጅግ አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ለሰዎች የሚትሰጠው አገልግሎት በመሆኑ እርካታዋ የላቀ ነው።

ዶ/ር ሊያ በጥቁር አንበሳ ሆስፒታል ሰራዋን እንደጀመረች የሚያጋጥማትን ፈተናዎች በብቃት በመቋቋምና በማለፍ አገልግሎቷን ስትሰጥ በተለያዩ ጊዜያቶች የሚታቀርባቸው ገለጻዎች እና ጥናታዊ ጽሁፎች በጤና ሚንስቴር ባልሞያዎች አድናቆትን አግኝታለች። በመቀጠልም ያላትን የሙያ ብቃት እና አቅም በመረዳት የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ዋና አስተዳዳሪ እንድትሆንም ተመርጣለች። ዶ/ር ሊያም በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል እና የጤና ኮሌጅ በአገልግሎት ዘመኑዋ በርካታ ለውጦችን አምጥታለች። “ተነሳሽነትን እና የሰራ ብርታትን በመናገር ሳይሆን በተግባር በማሳየት ፡ ለሰዎች የመስራት ነጻነትን በመስጠት እራሳቸውን ጠንካራ እንድያደርጉ ማገዝ ጥሩ ውጠት የሚያመጣ በመሆኑ መልካም ግንኙነቶችን መፍጠር እና በቡድን መስራት ውጠታማ አድርጎኛል” ትለናለች። በዚሁም በተለያዩ ማህበራቶች ቦርድ ውስጥ በመሳተፍ ወደ ስኬት ስታሸጋግር “ጥሪዬ ምርጧ የጤና ዶክተር ለመሆን ብቻ ሳይሆን በጤናው ዘርፍ ሰፊ ልህቀትን ለመፍጠርም ነው” እያለች በተግባር አሳይታለች። በቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል የህክምና ጤና ኮሌጅ ስትሰራ በዩኒቨርሲቲ ትምህርት ጊዜዋ የከነከናትን የሴት ተማሪዎች ቁጥር ማነስ በመቀየር በርካታ ሴት ተማሪዎችን በማነቃቃት በጤናው ዘርፍ እንድማሩ እና እንድሳተፉ አድርጋለች።

ከጥቅምት 28/2011ዓ.ም ጀምሮ የጤና ሚንስቴር ሚንስቴር ዲኤታ በመሆን ስታገለግል በመጋቢት 3/2012ዓ.ም የኢ.ፌ.ዴ.ሪ የጤና ሚኒስትር ሆናለች። የዓለም የጤና ሁነታ ፈተና ውስጥ በገባበት በዚህ ወቅት እርሷም የአገሯን ዜጎች ጤና ለማስጠበቅ ከኮቪድ-19 እና ለሎች የጤናው ዘርፍ ጉድለቶች ጋር ከፊት ለፊት በመሆን በመታገል ላይ ስትሆን በጥቅት ወራቶችም በጤናው በኩል ለውጦችን በማምጣት ላይ ትገኛለች።

ይህንንም የፈተና ጊዜ በድል ሰራዋን አጠናቃ የጤናውን ዘርፍ ወደ ተሻለ ደረጃ እንደምታደርሰው ዕምነታችን ነው። ስለ-ሷ አንስተን በእርሷ ጥንካሬ አምሳያነት እኛም ፈተናዎቻችንን በድል ለመወጣት እና ለወገን የሚተርፍ ሥራ ለመስራት እንበርታ!



ለሐ-ሷ 02 ግንቦት/2012 ዮታተመ

ለሁላችን

Mask Ethiopia



እናመሰግናለን!